አልልም  እንኳን አደረሰን

ታች አምና ነበረ ይህ አዲስ አመት
ይመጣል ይሔዳል በራሱ ጉልበት
ሁሉም ተለያይቶ በአገራው አንድነት
በማማ ኢትዮጵያ ሲያቅተው መኩራት
ችግር መከራ መናቆር እረክሰውበት
በጎሳ ክፍል በዘረኝነት
የተፈናቀለው የወገኔ ብዛት
ልክ እንደታችአምናው ሆኖ  የዛሬው  አመት
ምንም ለውጥ ሳይታይ እንዲሁ ዘልቆት
እንካን አደረሰ ለምን ትለዋለህ ብልህ አዲሱ አመት
እዛው ተቀምጦ ልክ እንደታች አምናው የዛሬውም አመት
በኢትዮጵያ ምድር መቸ አዲስ ሆኖ ያውቃል
የመጣ የሄደው ሲያስር ህዝብ ሲበድል
ብሎም ሲገድ ሲያስገድል
የእሳት ልጅ አረመጥ ሆኖ መጥቷል
ያየውንን ሁሉ ለኔ ለኔ የሚል
እንኳን አደረሰ አትበሉኝ ለአዲስ አመት
የሀገር  ሉአላዊነት ፈተና ከተውት
እንዲያው ለአፍ ብቻ ብል አዲስ አመት
እዛው ተዘፍቀው በዘላለም ስተት
በርስበር ጥላቻ በሴራ ክፉት
አልልም አዲስ አመት
የትኛው ነው ለውጡ ምሳሌው ያዲሱ
የሰው ጭንቅላቱ ወይንስ ነው ልብሱ
እኔስ አልገባኝም ይህ አዲስ አመት
ህዝብ እየተቸገረ በሰብአዊ ጥሰት
ሽርጉድ እያልኩኝ ባስመሰል አዲስ አመት
"ወገን አይነፋም " ካልቆምን በአንድነት
ይብቃን ይበቃናል ማስመሰል ውሸት
ኢትዮጵያን ለብሰን
ኢትዮጵያን ታጥቀን
በፍቅር ውቂያኖስ ሁላችን ተጠምቀን
የዘረኝነት ሸንኮፍ እላያችን ላይ ገፈን
እጅለጅ ተያይዘን
የእውነቱን አዲስ አመት ያኔ እናከብራለን
ሁላችን አንድ ሆነን
ለኢትዮጵያ ዘብቆመን
እርአይ ታጥቀን
ግና እውሸት አሉባልታ በባዶ አስኮፍሶን
በማስመሰል ብቻ እንደታች አምናው ከደገምነው ዛሬን
አልልም በፍፁም እንካን አደረሰን ፡፡

ቴዲ 11/09/19